# በግንባታ ጣቢያ ዙሪያ ከፍተኛ የደህንነት ጠቃሚ የምክር ጥቆማዎች

*የግንባታ ደህንነት የሁሉም ሥራ ነው*

የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) የኛን የግንባታ ሥራ ጣቢያዎችን ለሠራተኞች፣ ለሠራተኞች ቡድኖች እና ለሕዝብ ደህንነት የተጠበቀ እንድሆን ጠንክሮ ይሠራል። በግንባታው ወቅት ከባድ ማሽኖች፣ መሣሪያዎች እና ቁሳቁሶች አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት እነዚህን የደህንነት ምክሮች እንዲከተሉ እንጠይቃለን።

## አጠቃላይ ጠቃሚ የምክር ጥቆማዎች

- በተቻለ መጠን በግንባታ ዞን አቅራቢያ ከመሄድ ይቆጠቡ።
- ከሥራ አባላት እና ከጠቋሚዎች ሁሉንም የትራፊክ ምልክቶች እና አቅጣጫ ይከተሉ።
- ንቁ ይሁኑ እና በግንባታ ዞን ውስጥ ወይም አቅራቢያ በሚሆኑበት ጊዜ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ያስወግዱ።

## አሽከርካሪዎች/ተሳፋሪዎች



- እባክዎን በግንባታ ቦታ ዉስጥ አያሽከርክሩ። የግንባታ ሠራተኞችን ሆነ ራስዎን የመጉዳት አደጋ ስጋት ይፈጥራሉ። ወደ ቤት ወይም ንግድ ለመግባት በስራ ዞን ውስጥ መንዳት ካለብዎት እባክዎን ይጠንቀቁ እና የጣቢያ ሰራተኛውን መመሪያ ይከተሉ።
- ከቤትዎ/ ግቢዎ መግቢያ መውጫ ወደኋላ በሚወጡበት ጊዜ የግንባታ እንቅስቃሴዎች ወይም መሣሪያዎች በመንገዱ ላይ እንዳሉ ያረጋግጡ።
- የመንገድዎ ወይም የቤትዎ/ ግቢዎ መግቢያ መውጫው ከታገደ፣ ሥራ ከመጀመሩ በፊት መኪናዎን ከግንባታ ቦታ ውጭ ለማንቀሳቀስ/ ማውጣት ያስታውሱ።

## እግረኞች

- ቀስ ይበሉ እና የት እንደሚራመዱ፣ እንደሚሽከረከሩ (ተሽከርካሪ ወንበር ወይም መራመጃ) ወይም ብስክሌት የሚነግርዎን/ የሚያሳዩ ምልክቶችን ይከተሉ።
- ለግንባታ የጭነት መኪናዎች እና ማሽነሪዎች ይቁሙ፣ ይመልከቱ እና ያዳምጡ። በአቅራቢያው ካሉ አሽከርካሪው እርስዎን ማየቱን ያረጋግጡ።
- ያልተስተካከለ የእግረኛ መንገድ ወይም ዱካዎች እንዳሉ ይመልከቱ።
- ልጆች በግንባታው አካባቢ እንዳይራመዱ፣ እንዳይሮጡ፣ ብስክሌት እንዳይነዱ ወይም እንዳይጫወቱ ያስታውሷቸው።
- በግንባታ ቦታዎች ዙሪያ ሲሆኑ ሁሉንም የቤት እንስሳት በሊሽ/ መንትቻ ላይ ያቆዩ።

## ተደራሽነት

የተደራሽነት እና ሌሎች የመዳረሻ ፍላጎቶች ካሉዎት እነሱን ለማሳወቅ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (SPU) ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጁን ያነጋግሩ።

*ወደ ቁፋሮ ወይም የግንባታ ጣቢያ የግንባታ ሠራተኞቹን ለማነጋገር እባክዎን አይቅረቡ። ማንኛውም ከግንባታ ደህንነት ጋር የተዛመዱ ጥያቄዎች ወይም አስተያየቶች ካሉዎት እባክዎን በተቀበሉት የፕሮጀክት ማስታወቂያ ላይ ባለው ቁጥር/ኢሜል በኩል ያግኙን።*

*ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን :* [www.seattle.gov/utilities/constructionsafety](www.seattle.gov/utilities/constructionsafety) *ይጎብኙ*

**የግንባታ ጣቢያችንን ደህንነት የተጠበቀ እንድሆን ስላገዙን እናመሰግናለን!**